## እንድሪያስ እሸቴ ራሱን ስቶ ወድቆ ተገኘ፣ ግማሽ ሰውነቱም በድን ሆኖ ወደ አሜሪካ ለህክምና ተጓዘ

**ሚያዝያ 1፡ 2000 ዓ. ም. - ለመለስ ዜናዊ ታማኝ አገልጋይ ሆኖ የኢትዮጵያን ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በማፈራረስ ላይ የነበረው የአዲስ አበባ ዩኒኗርስቲ ፕሬዚዴንት ፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ መኝኝታ ቤቱ ውስጥ ራሱን ስቶ ወድቆ በቤት ሰራተኛው በመገኘቱ በአስቸኳይ ወደጦር ሃይሎች ሆስፒታል ተወስዷዋል፡፡ በሽታው የሚያሰጋ በመሆኑም በልዩ አውሮፕላን ወደ ዱባይ ተወስዶ ከዚያም ወደ አሜሪካ መጉዋዙ ሊታወቅ ችሉዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜም ከፊል ሰውነቱ በድን መሆኑ ታውቁዋል፡፡ ይህ ላመታት ከባድ አጫሽ፣ ሃይለኛ ጠጪና አደንዛዥ ዕፅም ተጠቃሚ ነው የሚባል ግለሰብ በአሁኑ ጊዜ ሁኔታው አስጊ መሆኑ ቢገለፅም ይትረፍ አይትረፍ ወይም እንደ ጉዋደኛው ዳዊት ዮሐንስ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ይቅር አይቅር ግልፅ አይደለም፡፡**

**እንድሪያስ እሸቴ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ ከአብዱል አባ ቦራና ሰባት ሌሎች ጋር ሆኖ በ1983 ወደለንደን በመሄድ ለመለስ ዜናዊ የመጀመሪያ ድጋፍ ሰጪ ሆኖ ራሱን ያጋለጠ ግለሰብ ሲሆን ከኤርትራ የተፈናቀሉትን የሀገር ዜጎች በተመለከተም የሰጠው «ሰያንሳቸው ነው!» የሚል አሳፋሪ መግለጫ በሕዝብ ያስደመጠውና ጥላቻን ያተረፈለትም መሆኑ ይታወቃል፡፡ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የአፈና እርምጃዎችን ሲያስወስድም ጥላቻን በማትረፉ የወያኔ አገዛዝ የግል ጠባቂዎች መድቦለት ሲታጀብ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ እንድሪያስ እሸቴ እና መሰል ጉዋደኞቹ በአዲስ አበባ አንድ የምሽት ቡና ቤት ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ግማሸ ራቁት የተደረጉ ሴት ልጆችን ሲያባልጉና አደንዛዥ ዕፅም ሲያጤሱ በፖሊስ ተይዘው በመለስ ትዕዛዝ መለቀቁም ይታወሳል፡፡ የገዢው ቡድን አባላትና ቅጥረኞች ሲታመሙ በሕዝብ አይሮፕላንና ወጪ በአስቸኩዋይ ወደ ባዕድነሀገር ተልከው ሲታከሙ ሰፊው ሕዝብ ግን መሰረታዊ የህክምና እንክብካቤ አጥቶ በማለቅ ላይ መሆኑንም ያጤኑዋል ይላሉ ታዛቢዎች፡፡**